Immigratie- en Naturalisatiedienst
Ministerie van Justitie en Veiligheid

# እዚህ እንድትኖር የማትፈለግ ባዕድ ነህ መባልህ ለአንተ ምን ትርጉም አለው?

ከኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት (IND) እዚህ እንድትኖር የማትፈለግ ባዕድ ነህ የሚል ውሳኔ ተሰጥቶሃል። በተሰጠህ ውሳኔ ላይ የማትፈለግ ባዕድ ነህ ተብለህ የተፈረደብህ በምን ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ይህ ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል ውሳኔ ምን እንደሆነ ኣና ለአንተ ምን ትርጉም እንዳለው ታነባለህ።

1. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔ ምንድን ነው?
2. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?
3. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምን ማለት ነው?
4. ስላንተ የሚገልጹ መረጃዎች ከ E&S እና SIS የተባሉት የመረጃ ስርዓቶች የሚሰረዘው መቼ ነው?
5. ያልተፈለገ ባዕድ ተብለህ እያለ ኔዘርላንድ ውስጥ ብትኖርስ ምን ይደረጋል?
6. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔን የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላላህ?
7. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?
8. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔን (ግዝያዊ) እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?
9. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?

## 1. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔ ምንድን ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ በሚለው ውሳኔ ውስጥ ኣንተ በኔዘርላንድ እንድትኖር እንደማይፈለግ ይገለጻል። ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ የሚሰጥህ IND ኣንተ ለኔዘርላንድ አደገኛ ነህ ብሎ በሚያምንበት ግዜ ነው። ይህ እርምጃ ብዙውን ጊዜ ከባድ ወንጀል በፈጸሙ ሰዎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ነው። ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው ውሳኔ ከተሰጠህ ወዲያውኑ ከኔዘርላንድ መውጣት ኣለብህ። ከዚያ በኋላ ወደ ኔዘርላንድ መግባት አይፈቀድልህም። ደግሞም ያልተፈለገ ባዕድ እንደተባልክ በመረጃ ስርዓት ውስጥ ይመዘገባል። ጥያቄ ቁጥር 3 ውስጥ ይህ የመረጃ ስርዓት ምን ማለት እንደሆነ ማብራርያ ታገኛለህ።

## 2. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?

ያልተፈለገ ባዕድ በሚለው መግለጫ ተግባራዊነቱን የሚያበቃበት ቀን የሌለው ሲሆን የሚቆመው IND ይህን ለማድረግ ሲወስን ብቻ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው ውሳኔ እንዲሰረዝልህ ራስህ ከጠየቅክ ብቻ ነው። ጥያቄ ቁጥር 8 ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ የሚለው ውሳኔን እንዲሰረዝልህ እንዴት መጠየቅ እንደምትችል ማብራርያ ታገኛለህ።

## 3. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምን ማለት ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ ነህ ከተባልክ መንግሥት ኣንተን በመረጃ ሥርዓት ውስጥ ያልተፈለገ ባዕድ እንደሆንክ ይመዘግበሃል። በዚህ መንገድ መንግስት ኣንተ ያልተፈለግክ ባዕድ እንደሆንክ ለማወቅ ይችላል ማለት ነው። በዚህ መንገድ ፖሊሶችና ድንበር ጠባቂዎች ኣንተ ያልተፈለገ ባዕድ እንደሆንክ እዛ የመረጃ ሥርዓት ውስጥ ማየት ይችላሉ። ከፈተሹህ በኋላ ድንበር ላይ ሊያስቆሙህ ይችላሉ፣ እናም ወደ'ዛ ኣገር እንድትገባ ኣይፈቅዱልህም። በሚሰጥህ የውሳኔ ጽሁፍ ላይ ኣንተ በየትኛው የመረጃ ሥርዓት ውስጥ እንደተመዘገብክ ይገለጻል።

2 የመረጃ ስርዓቶች አሉ፥

- Executie & Signalering (E&S): ይህ የኔዘርላንድ ፖሊሶችና ድንበር ጠባቂዎች የሚጠቀሙበት የመረጃ ሥርዓት ነው።
- Schengeninformatiesysteem (SIS): ይህ የኣውሮጳ የመረጃ ስርዓት ሆኖ የሸንገን ሀገራት የድንበር ጠባቂዎች እና ፖሊሶች የሚጠቀሙበት የመረጃ ሥርዓት ነው። የሼንገን አገሮች የትኞቹ እንደሆኑ በ www.ind.nl/schengengebied ወይም www.ind.nl/schengenarea ላይ ማንበብ ትችላለህ።

በ1 የመረጃ ስርዓት ውስጥ ብቻ ነህ መመዝገብ የምትችለው።

## 4. ስላንተ የሚገልጹ መረጃዎች ከ E&S እና SIS የተባሉት የመረጃ ስርዓቶች የሚሰረዘው መቼ ነው?

ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ማመልከቻ ያቀረብክ ከሆነ እናም ማመልከቻህን ተቀባይነት ካገኘ ሊሰረዝ ይችላል።

### 5. ያልተፈለገ ባዕድ ተብለህ እያለ ኔዘርላንድ ውስጥ ብትኖርስ ምን ይደረጋል?

ያልተፈለገ ባዕድ ነህ የሚል ውሳኔ ከተሰጠህ በኋላ ኔዘርላንድ ውስጥ መኖር በህግ ያስቀጣል። እስከ 6 ወር የሚደርስ የእስራት ውሳኔ ሊፈረድብህ ይችላል ወይም በሺዎች ዩሮ የሚቆጠር የገንዘብ ቅጣት ልትቀጣ ትችላለህ። ይህም በወንጀል መቅጫ ሕጉ በአንቀጽ 197 ላይ በዝርዝር ተገልጿል።

### 6. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔን የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ተቃውሞህን ወደ IND ማቅረብ ትችላለህ። በተሰጠህ ውሳኔ ውስጥ ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምትችል ተገልጿል።

### 7. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?

IND ያልተፈለገ ባዕድ የሚለውን ውሳኔ ካነሳልህ እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት ትችላለህ። ይህ የሚሆነው ኣንተ ራስህ እንዲነሳልህ ከጠየቅክ እና ማመልከቻህን በ IND ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው።

### 8. ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔን (ግዝያዊ) እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?

ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ። በጣም ልዩ እና አስቸኳይ በሆኑ ሁኔታዎች ያልተፈለገ ባዕድ የሚለውን መግለጫ ግዝያዊ እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ። ይህንን ለማድረግ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ወይም የመግባት እገዳ እንዲነሳልህ ለመጠየቅ የምትሞላውን ፎርም (9004 ወይም 9504) መሙላት ኣለብህ። ይህ ፎርም በድረ-ገጾን ማግኘት ትችላለህ። ፎርሙን በመሙላት ወደ IND መላክ ኣለብህ።

ሌላ ሰው ኣንተን በመወከል ያልተፈለገ ባዕድ የሚል ውሳኔን እንዲነሳልህ ሊጠይቅልህ ይችላል። ይህ ለማድረግ ግለሰቡ ኣንተን ወክሎ እርምጃ እንዲወስድ ኣንተ ሕጋዊ ፈቃድ መስጠት አለብህ። ይህንን ወረቀት ላይ በማስፈር ፊርማህን በማኖር ነው የምታደርገው። ይህ ውክልና ስልጣን ተብሎ ይጠራል።

### 9. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?

- www.ind.nl/ongewenstverklaring ወይም www.ind.nl/en/undesirability የሚሉ የኛ ድረ ገጾች ጎብኝ።
- ወደ የ IND የመረጃ መስመር፣ ስልክ ቁጥር +31 88 043 04 30 ደውል። ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 09:00 ሰዓት እስከ 17:00 ሰዓት ድረስ ባለው ግዜ መደወል ትችላላችሁ።

*ከዚህ ጽሑፉ ይዘት ምንም ዓይነት መብት ማግኘት አይቻልም። ትርጉሙ ወደ ትርጓሜ ልዩነት የሚያመራ ከሆነ በኔደርላንድስ ቋንቋ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ነው ወሳኝ የሚሆነው። ምንጬ በመጥቀስ እዚህ እትም ላይ የሚገኘውን ጽሑፍ ለሌላ ጥቅም ሊውል ይችላል።*